# Midroc Newsletter

79

A BI-MONTHLY PUBLICATION OF THE OFFICE OF THE CHIEF EXECUTIVE OFFICER

This Newsletter provides customers, employees, suppliers, shareholders and the community at large with current information on major performance and other activities of the companies under the leadership of the CEO

Volume 15, Issue No. 79

September — October 2014


## From the Chairman File

Over the years, MIDROC Ethiopia Group Companies have done considerably well in their specific areas of investment and have continued to expand their investment activities to achieve a higher level of return and most importantly be able to contribute to the



rapid economic development of Ethiopia. One of my major objectives is to adopt effective and sustainable business practices, which could be seen as models and be replicated by other private sector operators for their own benefit and for the benefit of our country.

## ቲ.ኤን.ኤ መደበኛ የአገር ውስጥ የበረራ አገልግሎት ጀመረ




*ሲኢኦ መደበኛ በረራውን በይፋ ሲያስጀምሩ*

ትራንስ ኔሽን ኤርዌይስ ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር (ቲ.ኤን.ኤ) በአገር ውስጥ መደበኛ በረራ ላይ ለመሠማራት ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ባገኘው ፈቃድ መሠረት ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ.ም. በይፋ መደበኛ በረራ ጀመረ፡፡

ኩባንያው በሣምንት ሁለት ቀናት ሰኞና ዓርብ መደበኛ በረራውን የሚያደርግ ሲሆን ሰኞ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ባሕር ዳርና ጐንደር የደርሶ መልስ ጉዞ ሲያደርግ የአርብ በረራ ከአዲስ አበባ ባሕር ዳር ጐንደርና ሑመራ ይሆናል፤ የመደበኛ በረራ አውሮፕላን ኦፕሬተር በሆነው ትራንስ ኔሽን ኤርዌይስ


*ወደ ገጽ 2 ዞሯል*


በውስጥ ገጾቻችን


- የ2006 ዓ.ም. ተጽእኖ ፈጣሪ እና አርአያ ግለሰብ............2
- ድንቅ ኢትዮጵያዊ ለውጥ አምጪ በሚል........................3
- የቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች የደመራ በዓል.................3
- የሰንደቅ ዓላማ ቀን ተከበረ.............................................4
- የቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች በዓለም አቀፍ..................4


Inside Pages


- የመቻሬና የወልድያ እግር ኳስ ቡድን የወዳጅነት............4
- ዘገባ ከሲኢኦ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል............................5
- From Employees File...............................................6
- ጠቅላላ ዕውቀት...........................................................7
- መልዕክት፣ ከቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር.......................8

# ቲ.ኤን.ኤ መደበኛ ...

አገልግሎት መጀመር በክልሉ የሚገኙትን የቱሪስት መስህብ ሥፍራዎች የበለጠ ለማስተዋወቅና በአየር ትራንስፖርት የተቀላጠፈ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል መሆኑ ተገልጿል፡፡

የበረራ ፕሮግራሙን ለማስጀመር በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ በአዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የተገኙት የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲብ ኦፊሠር ዶ/ር አረጋ ይርዳው ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ቀጥሎ በግል አየር መንገዱ በመደበኛነት የበረራ ፕሮግራም መጀመሩ አገሪቱ እያካሄደች ያለውን ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ የተቀላጠፈ እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡

መደበኛ በረራው በይፋ በተጀመረበት ዕለት የአገር ውስጥ መገናኛ ብዙሀን ሠራተኞችና የኩባንያው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ከአዲስ አበባ ባህር ዳርና ጐንደር ጉዞ ያደረጉ ሲሆን፤ በጐንደር ላንድ ማርክ ሆቴል በተዘጋጀው የአቀባበል ሥነ-ሥርዓት ላይ የጐንደር ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ፀጋዬ ነጋ ከተመረጡት የጉዞ መስመሮች ውስጥ ታሪካዊቷ ከተማ ጐንደር በመካተቷ መደሰታቸውን ገልፀው ለቀጣይ ሥራ መቃናት መስተዳድሩ እገዛ እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል፡፡

ኩባንያው በነበሩት ሁለት ዘመናዊ ዳሽ 8 አውሮፕላኖች በሩዋንዳ፣ በሱዳንና በሊቢያ በረጅም ጊዜ ኪራይ ሲሰራ የቆየ ሲሆን፤ ቀደም ሲል በ20 መንገደኞች ብቻ ተጥሎ የነበረው ገደብ በመነሳቱና ወደ 50 ከፍ በማለቱ በአገር ውስጥ አገልግሎት ለመሠማራት ችሏል፡፡

ትራንስ ኔሽን ኤርዌይስ ሁለት እያንዳንዳቸው 37 መንገደኞችን የሚይዙና ዕቃ ለመጫን የሚያገለግሉ የካናዳ ስሪት ዳሽ 8 አውሮፕላኖች ያሉት ሲሆን፣ ለሰብል መድኃኒተ መርጫ የሚያገለግል ተርቦ ትራሽ አውሮፕላን እንዲሁም ለማዕድን ፍለጋ፣ ለአካባቢ ጥናት፣ ለኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ፍተሻና ለቱሪስቶች ማጓጓዣ የሚያገለግል ሄሊኮፕተር በመጠቀም አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡




*ወ/ሮ ዕፀሕይወት ድንቁ ፕሪንሲፓል ኦፕሬሽን ኦፊሰር መደበኛ በረራው ሲጀምር በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ*

## ዶ/ር አረጋ ይርዳው የ2006 ዓ.ም. ተጽእኖ ፈጣሪ እና አርአያ ግለሰብ በመባል ተሸላሚ ሆኑ

ኢት-ባሕል ፕሮሞሽን ሰርቪስ ጥቅምት 1 ቀን 2007 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሆቴል አዳራሽ ባዘጋጀው የ2006 ዓ.ም. ተጽእኖ ፈጣሪ እና አርአያ ግለሰቦችን ዕውቅና የመስጠት ፕሮግራም ላይ ዶ/ር አረጋ ይርዳውን በረጅም ዓመት የሥራ አመራር ስኬት በሚል በዕለቱ ዕውቅና ሰጥቷቸዋል፡፡

በዚህ ልዩ ፕሮግራም በሚኒስትር ማዕረግ የፕሬዚዳንት ልዩ አማካሪ የሆኑት አቶ አሰፋ ከሲቶ ፕሮግራሙን ሲከፍቱ በዓመቱ ውስጥ በሥራቸው ጎልተው በመታየት በመልካም ሥራቸው ለትውልድ አርአያ በመሆን ለሀገር ልማትና ብልጽግና የሚተጉ ሰዎችን ማመስገንና ማበረታት፣ ከተቻለም መሸለምና በጎ ሥራቸውን እውቅና መስጠት ዓይነቱና መጠኑ ቢለያይም በዓለም ሀገራት ሁሉ የተለመደና የተወደደ ተግባር ነው፡፡ በሀገራችንም በኩልም በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፍ ላይ በመሠማራት በጎ ሥራቸው ጎልቶ በመታየት ሁሉም ሊመሰክርላቸው የቻሉትን ጠንካራና ምስጉን የሆኑትን ሰዎች በመለየት ጎልቶ የታየውን ሥራቸውን ለትውልድ አርአያ እንዲሆን እንደዚህ ዓይነቱን የእውቅና ፕሮግራም ማስተዋወቅና ማመስገን ተገቢ በመሆኑ አቅም በፈቀደ መጠን በመንግሥትም ሆነ በግል ተቋማት ደረጃ እውቅና የመስጠት ተግባሩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አሳስበዋል፡፡ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሕዝብ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ገዛኸኝ አባተ እንደገለጹት ወደፊትም በሀገራችን በልዩ ልዩ ዘርፍ ለአርአያነት የሚበቁ ሰዎችንና ሥራዎቻቸው እውቅና የሚያገኙበትና የሚሸለሙበትን ሥርዓት ለመፍጠር በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኩል በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በዕለቱም የ2006 ዓ.ም. የዓመቱ ተሸላሚ ለሆኑት በረጅም ዓመት የትምህርት ስኬትና በሥራ አመራር የተካኑትን የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲብ ኦፊሰር ለዶ/ር አረጋ ይርዳው የተሰጣቸውን ሽልማት በተወካያቸው በወ/ሮ ፍሬህይወት ዕንቁሐዋሪያት አማካኝነት እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ በዚሁ ዕለት የመቄዶኒያ የአረጋዊያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል መሥራች የሆኑትን አቶ ቢንያም በለጠ፣ እውቁ የኢትዮ - ጃዝ ባለሙያ አቶ ሙላቱ አስታጥቄ፣ በሕብረት የንግድ ሥራን በመሥራት ውጤታማ የሆኑት ሻለቃ ዓለማየሁ አምደማርያም እና የመቶ አለቃ ለማ አሰፋ፣ የመካከለኛና የረጅም ርቀት ሯጭ አትሌት ገንዘቤ ዲባባ፣ በስፖርት እና በተለያዩ ሥራዎች ላይ የላቀ ተሳትፎ ያደረጉት የአቶ ዮሐንስ ከበደ እና ከቀን የጉልበት ሠራተኛነት እስከ ባለ ሦስት ኮከብ ሆቴል ባለቤትነት ለደረሱት አቶ ኃይለሚካኤል ሙሉጌታ የሽልማት አሰጣጥ ተካሂዷል፡፡

በቀጣይም በኢትዮ ባህል ፕሮሞሽን ሰርቪስ የተዘጋጀው ‹‹ሐገረሰብ አርአያ›› መጽሔት በዓመት አንድ ጊዜ የሚወጣ እና የየዓመቱን አርአያ ግለሰቦችና ድርጅቶችን የህይወት ተሞክሮ የሚዳስስ መጽሔት ለመጀመሪያ ጊዜ የተመረቀ ሲሆን፣ መጽሔቱም የ2006 ዓ.ም. የተሸላሚዎች የግል ሕይወትና የስኬት ጉዞ ትውልድ እንዲማርበት በሰፊው ለአንባቢያን የቀረበ ነው፡፡



# ‹‹ድንቅ ኢትዮጵያዊ ለውጥ አምጪ›› በሚል የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ዶ/ር አረጋ ይርዳው ልዩ ሽልማት አገኙ




‹‹ቅድሚያ ለኢትዮጵያውያን›› በሚል መርህ ጥቅምት 13 ቀን 2007 ዓ.ም. በወሽምያ ክትፎና የባህላዊ የሥርግ አዳራሽ በተካሄደው ሥነሥርዓት በሀገራችን ዕድገትና የለውጥ ጉዞ ትልቅ አሻራ ያስቀመጡ ሰዎችን፣ በተሰማሩበት መስክ የወገንን የድህነትና የበታችነት ቀንበርን በመስበር አብዛኛው ሕብረተሰብ ዘንድ አመርቂ ለውጥ ለማስረፅ፣ የአመራር ብቃት ያመጡ 51 ድንቅ ኢትዮጵያውያንን በተምሣሌነት በመምረጥ የታላቋ ኢትዮጵያዊ 24 መርጃ ማዕከል ድርጅት ልዩ ሽልማት እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡

በተለይም ከተሸላሚዎቹ ውስጥ የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ዶ/ር አረጋ ይርዳው በኢትዮጵያ ውስጥ ሀገር በቀል ኩባንያዎች በመምራት ሠርቶ በማሠራት በብቃታቸውና ባልተለመደ መልኩ ሃያ የቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎችን በአንድ የአሠራር ሥርዓት ውስጥ በመምራት ለሀገራችን፣ ለወገኖቻችን ጉልህና የሚታይ ብርቅና ድንቅ አርአያ ያለው ተግባር በመፈፀማቸው እንዲሁም ትልቁን አሻራ በሀገራችን የለውጥ ጉዳና አትመው ያሳዩን ታላቅ መሪ መሆናቸውን በመግለፅ ‹‹ድንቅ ኢትዮጵያዊ ለውጥ አምጪ›› በሚል ማዕረግ የተሸለሙትን ሽልማት በተወካያቸው አቶ እስከአጥናፍ መዝገቤ፤ የኮርፖሬት ፐብሊክ ሪሌሽን ማኔጀር አማካኝነት እንዲደርሣቸው ተደርጓል፡፡ በወቅቱ ሽልማቱን የሰጡት በክብር እንግድነት የተገኙት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ አቶ አሠፋ ባህረ ሲሆኑ በዚሁ በዓል ላይ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ታዋቂ የመገናኛ ብዙሀን አባላት፣ የመንግሥትና የግል ተቋማት ኃላፊዎች እንደየአስተዋፅኦዋቸው ሽልማት ተቀብለዋል፡፡ ‹‹የታላቋ ኢትዮጵያ 24 መርጃ ማዕከል›› ለመጀመሪያ ጊዜ መቋቋሙን ምክንያት በማድረግ መረጃ ማዕከሉ ስድስት ያህል ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ማለትም በጤና በማህበራዊ በሚዲያ፣ በመዝናኛ፣ በትራንስፖርትና በኢንሹራንስ በመሣሠሉት ሥርነቀል የመረጃ ሥርዓት በማደራጀት ለአገልግሎት ዝግጁ መደረጉን የድርጅቱ ኤግዚኪዩቲብ ዳይሬክተር ገልፀዋል፡፡

# የቴክኖሎጂ ግሩፑ ኩባንያዎች የደመራ በዓልን አከበሩ

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች ሠራተኞች የመስቀል ደመራ በዓልን በታላቅ ድምቀት አከበሩ፡፡

በመቻሬ ኮርፖሬት ሴንተር ግቢ መቻሬ ሜዳ መስከረም 16 ቀን 2007 ዓ.ም. የተከበረውን የደመራ በዓል ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላ.የተ.የግ.ማ ሙሉ ዝግጅቱን ያዘጋጀ ሲሆን፤ የየኩባንያዎቹ ሥራ አስኪያጆች በኩባንያዎቹ ቁጥር ልክ የተዘጋጀውን ዳቦ ቆርሰው የችቦ ማብራት ሥነ ሥርዓት ተከናውኗል፡፡

በበዓሉ ላይ የተገኙት የሚድሮክ ኢትዮጵያ ሲኢኦ ዶ/ር አረጋ ይርዳው በዓሉ የሰላምና የደስታ እንዲሆን በመመኘት በአዲሱ ዓመት ኩባንያዎቹ የተሻለ የሥራ አፈፃፀም እንዲያሳዩ ሠራተኞች ተግተው መሥራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡









# የሰንደቅ ዓላማ ቀን ተከበረ



የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች የሰንደቅ ዓላማ ቀንን በድምቀት አከበሩ፡፡

በመላ አገሪቱ ለሰባተኛ ጊዜ በታላቅ ድምቀት የተከበረውን ይህንኑ በዓል መቻሬ ሜዳ በሚገኘው ኮርፖሬት ሴንተር የሚገኙ ሠራተኞችና የማኔጅመንት አባላት ሰኞ ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ.ም. ከጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ሰንደቅ ዓላማ በመስቀል አክብረዋል፡፡

## የቴክኖሎጂ ግሩፑ ኩባንያዎች በዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኤግዚቢሽን ላይ ተካፈሉ

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች አባል የሆኑት ኮምቦልቻ ብረታ ብረት ምርቶች ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ.ማ.፣ ዘመናዊ የህንፃ ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ.ማ.፣ ዋንዛ ፈርኒሺንግስ ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ.ማ.፣ አዲስ ሆም ዴፖ ኃላ.የተ.የግ.ማ. እና ሁዳ ሪል እስቴት ኃላ.የተ.የግ.ማ. ከመስከረም 7 እስከ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. በቆየው በ11ኛው ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኤግዚቢሽን ላይ ተካፍለዋል፡፡

ኤግዚቢሽኑን በይፋ መርቀው የከፈቱት የኢትዮጵያ ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢኒስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ዮሴፍ ብሩ ሲሆኑ፣ 150 የውጭና 60 የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ተካፋይ ሆነዋል፡፡




ኤግዚቢሽኑ ሲጎበኝ

## የመቻሬና የወልድያ እግር ኳስ ቡድን የወዳጅነት ጨዋታ አካሄዱ

የመቻሬ እግር ኳስ ቡድንና ዘንድሮ በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ከፍተኛ ተወዳዳሪ ሆኖ ይቀርባል ተብሎ የሚጠበቀው የወልድያ እግር ኳስ ቡድን የወዳጅነት ግጥሚያቸውን ጥቅምት 8 ቀን 2007 ዓ.ም. በመቻሬ ሜዳ አካሂደዋል፡፡ በውጤቱም የወልድያ እግር ኳስ ቡድን 4 ለ 0 በሆነ ውጤት አሸንፎአል፡፡

የወልድያ እግር ኳስ ቡድን በፕሪሚየር ሊጉ ውድድር በአዲስ አበባ ስታዲየም ከደደቢት ቡድን ጋር በወልድያ ከተማ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የእግር ኳስ ቡድን ጋር፤ በአዳማ ከተማ ደግሞ ከአዳማ ከነማ ጋር ግጥሚያ አካሂዷል፡፡

የወልድያ እግር ኳስ ቡድን የበላይ ጠባቂ የሚድሮክ ኢትዮያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሠር ዶ/ር አረጋ ይርዳው በውድድር ቦታዎች በመገኘት ቡድኑን አበረታተዋል፡፡



# ዘገባ ከሲኢኦ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል

## በጨፋ፣ በደሴና በወልድያ ከተማ ከጥቅምት 21 — 23 ቀን 2007 ዓ.ም. የተከናወኑ የመስክ ሥራዎች

ዶ/ር አረጋ ይርዳው የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ጥቅምት 21 ቀን 2007 ዓ.ም የኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ አካል የሆነው የጨፋ እርሻ ልማት የሥራ እንቅስቀሴን የጎበኙ ሲሆን ከማኔጅመንቱና ሠራተኞች ጋርም ተወያይተዋል፡፡ የጨፋ እርሻ ልማት ዘንድሮ በጤፍ፣ በማሽላ፣ በፍራፍሬ፣ በእንስሳት ተዋፅኦና በመሳሰሉት የምርት ሂደቶች እየሰጠ የሚገኘው አገልግሎት እየተጠናከረ የመጣ በመሆኑ ሠራተኞቹን አበረታተዋል፡፡

ሲኢኦ በደሴ ከተማ የኩዊንስ ሱፐርማርኬት፣ የሁዳ ሪል እስቴትና በቅርቡ የተገዛውንና ሥራ የጀመረውን የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ህንፃና የሥራ እንቅስቃሴን የጎበኙ ሲሆን ሀጂ ሙሀመድ ያሲን የንግድ ማዕከል የመኝታ ክፍሎች፣ የሱፐር ማርኬት፣ የባንክ፣ የካፍቴሪያ፣ የኢንሹራንስና የመሳሰሉትን በንፅህና እየሰጡ የሚገኙትን አገልግሎቶች አድንቀዋል፡፡ በመቀጠልም ጉዞአቸውን ወደ ወልድያ ከተማ አድርገዋል፡፡

ጥቅምት 22 ቀን 2007 ዓ.ም በወልድያ ከተማ እየተገነባ ያለውን የሼህ ሙሀመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲንን ስታዲየም የጎበኙ ሲሆን ያለበትን ደረጃ ከተመለከቱ በኋላ መሠራት እና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡትን እንዲሁም የእያንዳንዱን ፕሮጀክቶች የሥራ ደረጃ፣ የገስት ሀውስ ግንባታ፣ የተጫዋቾች ልብስ መለወጫ ክፍሎች፣ መፀዳጃ ቤቶች፣ የፍሳሽ መውረጃ ፖሴቶችና አካባቢውን ተዘዋውረው ተመልክተዋል፡፡ በሙያው ላይ እየተሳተፉ ያሉትን ሠራተኞችም አበረታትዋል፡፡

በዚህ ዕለት በወልዲያ ከተማ ከቀኑ 9 ሰዓት በፕሪሚየር ሊግ 1ኛ ዙር የእግር ኳስ ውድድር ግጥሚያ የሚያደርጉትን የወልዲያ እግር ኳስ ቡድንና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እግር ኳስ ቡድንን በመልካ ቆሌ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት አጠገብ በሚገኘው የእግር ኳስ ሜዳ በመገኘት ከተጫዋቾች ጋር ተዋውቀው ጨዋታውን አስጀምረዋል፤ ጨዋታውንም ተከታትለዋል፡፡ ሲኢኦ በስታዲየም ሲደርሱ የነበረው ድባብ የተለየ ነበር፤ ‹‹ዶ/ር አረጋ ይርዳው›› እናመሰግናለን የሚል ባነር በመያዝና ‹‹ይገባዋል›› በሚል ትልቅ የደስታ ስሜት ሁሉም የስታዲየሙ ታዳሚ አክብሮቱንና ደስታውን በጭብጨባ ገልጾላቸዋል፡፡ የዚህ ምስጋና ምክንያት በሼህ ሙሀመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ስም እየተገነባ ያለውን ዋናውንና ዘመናዊ ስታዲየም ለ2007 እግርኳስ ውድድር ሊደርስ ስለማይችል በምትኩ በወልድያ ከተማ እግር ኳስ ቡድን ውጤት ያመጣውን ዕድል የከተማው ህዝብ እንዲጠቀምበት ለማድረግና የዕድሉም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የመልካ ቆሌ የእግር ኳስ ሜዳን ገጽታ በመለወጥ ለፕርሜየር ሊግ ውድድር ዝግጁ እንዲሆን በማድረጋቸው ነው፡፡ የመልካ ቆሌ የኳስ ሜዳ የነበረበት ሁናቴ ለጨዋታ አመቺ ስላልነበር የሜዳው አፈር ተወግዶ በምትኩ ሣር ሊያበቅል የሚችልና ለሜዳው አመቺ አፈር ከተተካና ከተደለደለ በኋላ ሣር እንዲተከልበት ተደርጎ አረንጓዴ መስክ የሚኖረውን ማራኪ ገጽታ እንዲይዝ ሆኗል፡፡




በተጨማሪም የጨዋታ ሜዳው ዙሪያ በሽቦ አጥር ተከልሏል፣ በቆርቆሮ ታጥሯል፣ የሜዳው አራቱ ማዕዘን ለተመልካች ምቹ እንዲሆን በደረጃ መልክ መቀመጫ ተዘጋጅቶለታል፣ በተለይም ክቡር ትሪቢውን በምሥራቅ በኩል ከፍ ተደርጎ መቀመጫ የተዘጋጀለት ሲሆን ጣሪያው በቆርቆሮ እንዲለብስ ተደርጓል፡፡ ለሁለት ቡድኖች የሚሆን የልብስ መለወጫ ክፍሎች ተሰርቷል፡፡ ታዲያ ይህን ሁሉ ሥራ በአጭር ጊዜ በቦታው ተገኝተውና ቆመው ያሰሩት ዶ/ር አረጋ ይርዳው ናቸው፡፡ የፀሀዩ ሀሩርና አቧራው ንፋሱ ሳይበግራቸው ለወልዲያ ከተማ ህዝብ ያላቸውን ወሰን የሌለው ፍቅርና አክብሮት የገለጹበት አንዱ ማሳያ በመሆኑና ህዝቡም ባገኘው አጋጣሚ ለእኚህ ታላቅ ሰው አክብሮቱን፣ ደስታውንና አድናቆቱን ልጅ፣ ወጣት፣ አዋቂ፣ ሴት፣ ወንድ ሳይል ከልቡ ምሥጋና ያቀረበበት አጋጣሚ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በማንኛውም ጊዜ ከወልዲያ ህዝብ ጎን ቆመው የሚያበረታቱንና፤ የዚህን ሁሉ ዕድል ፈጣሪና ፈር ቀዳጅ ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲንንና የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቤተሰቦች በአክብሮትና በልዩ የደስታ ስሜት የእናመሰግናለን መልዕክቱን በሆታ፣ በጭብጨባና በዕልልታ ገልጿል፡፡

ለእግር ኳስ ልዩ ፍቅር ያለው የወልዲያ ከተማ ነዋሪ በፕሪሚየር ሊግ የሚደረጉትን የእግር ኳስ ውድድሮች አገር ሳያቋርጥ በከተማው ቁጭ ብሎ ጨዋታዎችን ይከታተላል፡፡ በዕለቱ የወልዲያ እግርኳስ ቡድንና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እግር ኳስ ቡድን ጨዋታቸውን (0 ለ 0) በሆነ ውጤት ያጠናቀቁ ሲሆን ህዝቡ ጨዋነት በተሞላበት ሁኔታ ድጋፍ ሰጥቷል፡፡ ጨዋታው ምሽት 11፡30 ምሽት ሲጠናቀቅ ሲኢኦ እና በእርሳቸው የሚመራው ቡድን ወደ ደሴ ከተማ የመልስ ጉዞ አደረገ፡፡ በደሴ ከተማ ከምሽቱ 2፡00-4፡00 ሰዓት ለሁዳ፣ ለኩዊንስና ለዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች የእራት ግብዣ አድርገውላቸው ስለነበር ሁሉም ተገኝተዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ስለ እያንዳንዱ ኩባንያ የሥራ እንቅስቃሴ በወቅቱ ካለው የገበያ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ገለጻ አድርገውላቸዋል፡፡ ሠራተኞችም በቂ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የመቻሬ ከፍተኛ ክሊኒክ ቅርንጫፍ በደሴ ከተማ መክፈት እንደሚያስፈልግ ለዶ/ር አለባቸው ኃይሉ የክሊኒኩ ሜዲካል ዳይሬክተር ኃላፊነት የሰጡ ሲሆን በትምህርት በኩል ራስን ማጠናከር እንደሚስፈልግና ለዚሁም ፖሊሲዎቻችን እንደሚፈቅዱ ገልፀዋል፡፡ ሠራተኛውም እንደተለመደው የሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲሁም የዶ/ር አረጋ ይርዳውና ቤተሰቦቻቸውን ዕድሜና ጤና በመመኘት የፕሮግራሙ ፍፃሜ ሆኗል፡፡

ጥቅምት 24 ቀን 2007 ዓ.ም. ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት የመልስ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ተደርጎ ጧት 4፡00 ሰዓት መቻሬ ግቢ የደረሱ ሲሆን፤ በጉዞ ላይ የነበሩት የቡድኑ አባላት ወደየቤታቸው ሲሄዱ የዶ/ር አረጋ ይርዳው ጉዞ ግን አልተጠናቀቀም ነበርና በዚሁ ዕለት ምሽት ወደ አውሮፓ ለሚያደርጉት ጉዞ ቀጣይ ዝግጅት ለማድረግ ወደ ቢሮአቸው አመሩ፡፡

# Employees File - *New Appointment*

## ATO TARIKU NEGERA



Ato Tariku Negera, appointed as General Manager of ELFORA Agro Industries PLC effective October 6, 2014. Ato Tariku Negera holds MSC degree in Water Resources and Environmental Management by using Geographic Information System from ITC, Netherland and B.Sc degree in Geology from Addis Ababa University. He worked as General Manager of Oromia Water Works Construction Enterprise, as Deputy General Manager of Oromia Water Design and Supervision Enterprise and Deputy General Manager of Oromia Water Design and Supervision Enterprise and Deputy Bureau Head of Oromia Water, Mines and Energy Resources Development Bureau before joining MIDROC Gold Mine PLC at a capacity of Director of Special Projects.

At MIDROC Ethiopia Technology Group and under the MIDROC Gold Mine PLC, he has participated on supervision of ground water drilling at Metekel Gold Mine Project and Nettle Alfalfa Project and location selected of boreholes for Nettle Alfalfa project and Cheffa Farms of ELFORA Agro-Industries PLC. Ato Tariku Negera is married and is a father of a daughter and two sons.

## ATO SOLOMON DEJENE



Ato Solomon Dejene, appointed as General Manager of Trust Protection & Personnel Services PLC effective October 6, 2014. Ato Solomon Dejene holds B.A Degree in Accounting and currently finalizing his MBA studies at Unity University. He worked in various enterprises under the Ethiopian Retail Trade Corporation in different capacities: Accountant, Chief Accountant, and Division Head Planning & Statistics. He worked in Tabor Ceramics Factory PLC as a General Accounts Division head and finally as a Finance Manager. He also worked in Noah Transport Share Company in the capacity of Finance Manager.

Ato Solomon Dejene joined KOSPI in May, 1999 (G.C.) which is operating under the MIDROC Ethiopia Technology Group and served as a Finance Manager for seven (7) years. He, then, transferred to MIDROC Ethiopia Technology Group Corporate Office where he served as a Sr. Director, Corporate Finance & Material Management Services. During his stay in the corporate office, apart from coordinating the corporate Finance & Materials Management Services, he also involved in handling financial activities of various projects like ELFORA Alfalfa Project, MHA Stadium Project and DAT Glass Project.

## ATO YOSEPH ATSEBHA



Ato Yoseph Atsbeha appointed as Deputy General Manager of Day Light Applied Technologies (DAT) Plc. Ato Yoseph holds B.Sc degree in Mechanical Engineering from Bahir Dar University. He has worked as a Junior Mechanical Engineer in Addis Ababa Water and Sewerage Authority and as a Design Engineer in DAN Techno Craft PLC, Sales and Customer Service Engineer in WATT International PLC before joining Daylight Applied Technologies (DAT) PLC, as a Mechanical Project Engineer. During his stay at DAT, he had been involved in various activities of supervising and coordinating the erection, installation and commissioning of the Glass Bottles Project, After the commissioning task at DAT, he was promoted to the position of Manager of Maintenance Services. Later, he joined Wanza Furshings Industry PLC to serve as a Manager, Engineering & Technical Services.

Finally, he has been transferred to MIDROC CEO, Management and Leadership Services PLC to serve as a Manager, Corporate Engineering/ Technology Support, where he has contributed to the installation of the Crown Cork Factory at Daylight Applied Technologies PLC and the modernization effort that is being conducted to have a new $CO_2$ plant for addis Gas & Plastic Factory PLC to focus on growth and expansion. He also assigned as deputy general manager of Addis Gas & Plastic Factory PLC.

## ATO MICHAEL MITIKU



Ato Michael Mitiku appointed as Deputy General Manager of addis Gas & Plastics Factory PLC effective June 16, 2014. Ato Michael Mitiku holds B.Sc degree in Mechanical Engineering from Bahir Dar University. He worked as an Assistant Lecturer in Bahir Dar University Engineering Faculty; as Mechanical Engineer in Equatorial Guinea Top Real Estate; as an After-sales Service Engineer for Elevators, Escalators and Generators in SINTEC Ethiopia PLC; and as Senior Engineer for design and installation of HVAC system in TechTra Engineering PLC before joining MIDROC CEO, Management and Leadership Service PLC at a capacity of Senior Engineer in the department of Special Project Service and later as Manager of Corporate Engineering Technology Support.

At MIDROC Ethiopia Technology Group and under the CEO office, he has participated as lead engineer in the installation of the ELFORA Dip Irrigation system at Shallow, erection of the Crown Work Factory at DAT, and the evaluation and acquisition of the $CO_2$ Manufacturing Equipment for addis Gas and Plastics Factory PLC.

## ጠቅላላ ዕውቀት

# የሳምባ ነቀርሳ (ቲቢ)

የሳምባ ነቀርሳ (ቲቢ) ቲዩበርኪሎሲስ ባሲላይ በተባሉ በአየር ላይ መንሳፈፍ በሚችሉ ጥቃቅን ጀርሞች አማካኝነት በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፍ በሽታ ነው። በቲቢ የተያዘ ሰው በሚስልበት ወይም በሚያስነጥስበት ጊዜ፣ እነዚህ ጀርሞች ወደ አየር ይበተናሉ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ ጀርሞቹን ከአየር ጋር ስበው በማስገባት የቲቢ በሽታው ሊተላለፍባቸው ይችላል።

አብዛኞቻችን እነዚህን ጀርሞች በሳምባችን ይዘን እንኖራለን። ነገር ግን የጀርሞቹ በሳምባችን መኖር የቲቢ በሽተኛ ያደርገናል ማለት አይደለም። አብዛኞቹ ሰዎች ቲቢ ሳምባን ብቻ ያጠቃል ብለው ያስባሉ። ምንም እንኳን በቲቢ የተያዙ ሰዎች 70% በሳምባቸው ውስጥ ጀርሞቹ ቢገኙም፣ በተጨማሪ ቲቢ አጥንት፣ ጭንቅላት ወይም ልብን የመሳሰሉት የሰውነት ክፍሎችን ሊያጠቃ ይችላል።

ጀርሞቹ በሽታውን የሚያስይዙን ወይም የሚያስነሱት የሰውነታችን ተፈጥሯዊ የበሽታ የመከላከል ብቃት ሲደክም ነው። ድካም፣ ጭንቀት፣ ያልተመጣጠነ አመጋገብ፣ የተለያዩ ሱሶች ወይም ሌሎች በሽታዎች ይህንን የሰውነታችንን በሽታ የመከላከል ብቃት ያዳክማሉ።

ከቲቢ ዓይነቶች ሁሉ ሳምባን የሚያጠቃው ዓይነት በአብዛኛው የሚከሰተው ነው። ሆኖም ግን ጀርሞቹ ከሳምባ ጀምረው በደም ዝውውር ወደሌላ የሰውነታችን ክፍል በመዛመት የበለጠ ሊጎዱን ይችላሉ።

የተዳፈነ የቱበርኪሎሲስ ልክፍት በተጨማሪ “ድብቅ” ቲቢ ተብሎ ይጠራል። ምክንያቱም ጀርሞቹ ሰውነትዎ እስኪፋለማቸው ድረስ በድብቅ ይኖራሉ። የቲቢ ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ሊኖርዎት ይችላል። ሆኖም ግን ድብቅ ቲቢ ካለዎት የደረት ኤክስሬይ በመነሳት ማወቅ ይቻላል።

በክንድዎ ላይ የሚደረግ ቀላል ምርመራ የቲቢ ጀርም በሰውነትዎ ውስጥ መኖሩንና አለመኖሩን ሊያረጋግጥልዎት ይችላል። ፖዘቲቭ የሆነ የቲቢ የቆዳ ምርመራ ውጤት አብዛኛውን ግዜ የቲቢ ጀርም በሰውነትዎ ውስጥ መኖሩን ያረጋግጥሎታል። እንደ የደረት የራጂ /ኤክስሬይ/ ምርመራ ወይም የአክታ ምርመራ የመሳሰሉ ተጨማሪ ምርመራዎች ሊያስፈልግዎ ይችላል።

## የሳምባ ነቀርሳ ምልክቶች

የማያቋርጥ ማሳል፤ የመላ ሰውነት መድከም፤ በሌሊት ብዙ ማላብ (አየሩ ቀዝቃዛ ባልሆነበትም ጊዜ ጭምር)፤ የምግብ ፍላጎት መቀነስ ወይም መጥፋት፤ የሰውነት ክብደት መቀነስ፤ በደረት አካባቢ የሚሰማ ህመም፤ የትንፋሽ ማጠር፤ ደም የተቀላቀለበት አክታ ወይም ከሳል ጋር የሚወጣ ደም ማየት ናቸው።

## የሳምባ ነቀርሳ ሕክምና

የሳምባ ነቀርሳን (ቲቢን) ለማከም የሚረዱ የተለያዩ መድኃኒቶች አሉ። እነዚህም መድኃኒቶች ቢያንስ ለስድስት ወራት መወሰድ አለባቸው። የቲቢ በሽተኞች በሽታው ሥር ሳይሰድ ህክምና ከጀመሩ ሆስፒታል መተኛት የለባቸውም። ሆኖም በሽታው ከበረታ በኋላ ህክምና የሚጀምሩ በሽተኞች በጣም ሊደክሙ ስለሚችሉ ቢያንስ ለሁለት ወር ሆስፒታል መተኛት ሊጠበቅባቸው ይችላል። ከሁለት ወር በኋላ መድኃኒቱን በቤት እየወሰዱ ሊቆዩ ይችላሉ።

የሳምባ ነቀርሳ ጀርም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ መድኃኒቶች ሊጠፉ የማይችለው የቲቢ መድኃኒቶች በትክክል ካልተሰጠ ወይም ሳያልቅ ከተቋረጠ ነው። የቲቢ መድሃኒት ለስድስት ወር መወሰድ አለበት። ሆኖም በሽተኛው ስድስት ወር ሳይሞላው የተሻለው ሊመስል ይችላል። በሽተኞች የተሻላቸው ሲመስላቸው መድኃኒቱን ያቋርጣሉ። ይህ ደግሞ የቲቢ ጀርም እንደገና እንዲነሳ ያደርገዋል።

መድኃኒት ለመድ ቲቢ አንድ ሰው መድኃኒቱን በሚገባ ሳይወስድ ሲቀር፣ ወይም ሕክምናውን ሲያቋርጥ የቲቢ ሕዋሳት ያንን መድኃኒት ይለምዱትና ይጠነክራሉ። ይህም ሕመምተኛውም ከፊተኛው መድኃኒት ሌላ ጠንከር ያለ መድኃኒት ረዘም ላለ ጊዜ መውሰድ ይኖርበታል ማለት ነው። ሕመምተኛው የፊተኛውን መድኃኒት ሳያቋርጥ በወቅቱ ቢወስድ ኖሮ በተሻለው ነበር። መድኃኒት ለመድ ቲቢ ለማከም አስቸጋሪና ዋጋውም በጣም ውድ ነው።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተቀየረ የቲቢ ጀርም ልክ እንደተራው የቲቢ ጀርም በቀላሉ ከሰው ወደሰው ይተላለፋል። ህክምናውም እስከ 18 ወራት ድረስ ሊፈጅ የሚችል ሲሆን የመድኃኒት ዋጋውም በ20 እጥፍ ይጨምራል።

የሳምባ ነቀርሳ ኤች.አይ.ቪ. ያለባቸውን ሰዎች በጣም ያጠቃል። ኤች.አይ.ቪ. እንዳለብዎት የሚያውቁ ከሆነ እራስዎን ከሳምባ ነቀርሳ መጠበቅ አለብዎት።

# መልዕክት፣ ከቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር

## የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት አድማሳችንን ይበልጥ እናሰፋለን

እ.ኤ.አ. በ2004 ዓ.ም. የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች አባል የሆነው ትራንስ ኔሽን ኤርዌይስ (ቲ.ኤን.ኤ) በአየር ሰውንም ሆነ ዕቃን ለማጓጓዝ የተቋቋመ ኩባንያ ነው፡፡

በወቅቱ የግል የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች መንገደኞችን የማጓጓዝ አቅማቸው በ20 የተገደበ በመሆኑ የቲ.ኤን.ኤ አውሮፕላኖች መያዝ ከሚችሉት መንገደኞች አንጻር አዋጪ ሆኖ ባለመገኘቱ የኩባንያውን አውሮፕላኖች በሱዳን፣ በሊቢያና በሩዋንዳ አሠማርተን ሥራቸውን ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡

በአገራችን በግል አየር ማጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት ጅማሬ መኖሩ አበረታች ቢሆንም የመቀመጫዎች ቁጥር አነስተኛ መሆን በመስኩ ለተሰማራነው ፈታኝ ሁኔታ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመቀመጫዎች ቁጥር ላይ ተጥሎ የነበረው ገደብ ተነስቶ ወደ 50 ከፍ በመደረጉ ባሉን አውሮፕላኖች በግል የአየር መጓጓዣ ሥራ ለመሠማራት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልናል፡፡ በዚህም የመጀመሪያውን በረራችንን ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም. ለንግስ ወደ ድሬዳዋ ቁልቢ ለሚጓዙ ምዕመናን አገልግሎት ሠጥተናል፡፡

በቀጣይም ጥቅምት 2 እና 3 ቀን 2006 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ወደ ባህር ዳር ጉዞ በማድረግ በዚያ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎቻችንና የቱሪስት መስህቦችን የማስጐብኘት ሥራ ማከናወናችን ይታወሳል፡፡

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት የመስጠት ሥራችንን አጠናክረን በመቀጠላችን በአሁኑ ወቅት መደበኛ የበረራ መስመር ፈቃድ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን በማግኘት ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ.ም. በይፋ መደበኛ በረራ ጀምረናል፡፡

ይህ መደበኛ በረራችን በሣምንት ሁለት ቀናት እያከናወንን እንገኛለን፡፡ በዚህም መሠረት ሰኞ ከአዲስ አበባ ባሕር ዳር እና ጐንደር የደርሶ መልስ በረራ የሚያደርግ ሲሆን አርብ የሚያከናውነው በረራ ከአዲስ አበባ ባሕር ዳር ጐንደር እና ሁመራ ይሆናል፡፡ ይህም በረራ በተለይም በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የሚገኙትን ልዩ ልዩ የቱሪስት መስህቦችና ታሪካዊ ሥፍራዎች እንዲሁም ተጓዦች ለሚፈልጉዋቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ምቹ አገልግሎት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

በአገራችን የተጀመረውን ይህንን አዲስ የግል አየር መንገድ አገልግሎት ሥራ አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ለማድረግና የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ትብብር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

የእኛ የሆነው ትራንስ ኔሽን ኤርዌይስ (ቲ.ኤን.ኤ) በእስካሁኑ ተግባሩ በአገሪቱ በግሉ ዘርፍ ያልተለመዱ የማጓጓዣ አገልግሎት የመስጠት፣ በዘመናዊው ሄሊኮፕተራችን ለቱሪስቶች ማጓጓዣና ለአካባቢ የኤሌክትሪክ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ጥናት ለመሳሰሉት የሚሠጠውን አገልግሎት አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡



ዶ/ር አረጋ ይርዳው
Dr. Arega Yirdaw
ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር፣ ሚድሮክ ኢትዮጵያ
Chief Executive Officer, MIDROC Ethiopia

*Address:*
*MIDROC Ethiopia Technology Group*
*Office of the Chief Executive Officer,*
*Fax: +251-11-371-5988 / 372-4977*
*P.O. Box: 5787, Addis Ababa Ethiopia*
*E-mail: ceomidroc@ethionet.et*
*Website: www.midroc-ethiotechgroup.com*

በነፃ የሚታደል *(Distributed at no Cost)*